# ያሁኑ ይባስ

የአውሮፓ አሜሪካ ፣ ምስኪን ዲያስፖራ
በቀን አንድ ዶላር ፣ ተብሎ ሲጠራ
በአንድነት ቆሞ ፣ ተነስቶ በጋራ
ለወገኑ ደጀን ፣ ሊሆን ባላደራ
ያጎረሰ መስሎት ፣ ለደሃው እንጀራ
በትውልድ ሃገሩ ፣ ተቋም የሚሰራ
    መች ጠረጠረና ፣ ተንኮል እንዲሰራ
    በገዛ ገንዘቡ ፣ መከራ እንደዘራ
    ዘውግ እየመረጡ ፣ እየለዩ ጎራ
    ቡልዶዘር ገዙበት ፣ ወገኑን ምንጠራ ።

ሸጋ ሸጋ ቃላት ፣ ስለተናገረ
ከመቆለት አልፎ ፣ ወገን እያረረ
የቃሉን ተቃርኖ ፣ እየተገበረ
ፍየል ወዲህ ማዶ ፣ ቅዝምዝም ወደዚያ ፣
እያንሸዋረረ
ተሸውዷል ወገን ፣ ቃሉ ስላማረ ።

አዝሎ የመጣውን ፣ ደብቆ ከጀርባ
ኢትዮጵያዊነትን ፣ ቀለም እየቀባ
አገሬ የሚለውን ፣ ሆዱን እያባባ
ለዘውጌ ተግባሩ ፣ አረገው ሰለባ ፣
        እኛው አጨብጭበን ፣ አልብሰነው ካባ
        የሚዝናናበትን ፣ ፓርክ ሊገነባ
        በሴት ፣ በህፃናት ፣ ባዛውንቶች እንባ
        በነሱ ፊንፊኔ ፣ በኛ አዲስ አበባ
        ይሄው ባደባባይ ፣ ይሸረባል ደባ ።

እንዳለመታደል ፣ የርግማን ሆኖበት
አብይና ለማ ፣ ለሚናፈሱበት
የሺ ደሃ ጎጆ ፣ ሊፈርስ ግድ አለበት
ከጭቆና አገዛዝ ፣ አዙሪት ቀለበት
ሊወጣት አልቻለም ፣ ዛሬም አልሆነለት
ሁሌም ባለ ጊዜ ፣ አለ እንደሳቀበት ።

ትንሹን ትልቁን ፣ ዜጋ እያስለቀሰ
ጎጆውን በላዩ ፣ እያፈራረሰ
የሚቀበርበት ፣ ጉድጓድ እየማሰ
የሰው ልጅ ከእንሰሳ ፣ አንሶ እየረከሰ
ያሁኑ ይባስ እንጂ ፣ መች እንባው ታበሰ ።

በደም የታጠቡ ፣ ሺዎች የገደሉ
ሌባና ዘራፊ ፣ መቀሌ ላይ ያሉ
እስካፍንጫ ታጥቀው ፣ ግጠመን እያሉ
ጉልበትን በምስኪን ፣ ይለማመዳሉ
ወንድነቱ ካለ ፣ እነሱን ታገሉ
ዛሬም በዘረኞች ፣ ይብቃን መታለሉ ።

ታዛቢው

February 22, 2019